*የዩናይት ስቴት  እኩል የሥራ ዕድል  የማግኘት ኮሚሽን*

# *አድልዎን መከላከል መልካም ሥራ ነው*

***አድልዎን መከላከል መልካም የሥራ ስሜት ያመጣል።*** ለሕግ ተገዢ መሆን የሠራተኛውን ምርታማነት፣ ሥራቸውን መውደድ፣ እና ለስነልቦናቸው ከፍ የሚያደርግ ሲሆን ለሙግት የሚወጣውን ወጪ ይቀንሳል። የአካል ጉዳት ያለባችውን ግለሰቦች በመቅጠርዎ  ወይም ንግድዎን ለአካል ጉዳተኛ ግለሰቦች ዕድል በመስጠትዎ ለግብር ጥቅማ ጥቅም መብት ሊኖርዎት ይችላል! ለበለጠ መረጃ ይህን http://www.eeoc.gov/eeoc/publications/adahandbook.cfm#appendixa ድኅረገጽ ይመልከቱ።

***EEOC አነስተኛ የንግድ ባለቤቶችን ሊረዳ ይችላል።*** የEEOC ዘርን፣ የቆዳ ቀለምን፣ ሃይማኖትን፣ ጾታን፣ የትውልድ አገርን፣ የአካል ጉዳትን፣ ዕድሜን፣ እና የዘረግንድ መረጃን መሠረት በማድረግ የሚደረግ የሥራ አድልዎን የሚቃወመውን የፌዴራል ሕግን የሚያጠናክር የፌዴራል መንግሥት እጀንስ ነው።  እነዚህ ሕጎች  መድልዎን በመቃወም ወይም በማሳውቅ ወይም መድልዎን በመመርመር  ወይም በሕጋው መንገድ በመጠየቅ ውስጥ በመሳተፌ የሚመጣውን ጥቃት (ቅጣት) ይከለክላል።

## የእርስዎ ኃላፊነቶች

▪ የሥራ ዕድል ውሳኔዎች በዘር፣ በቆዳ ቀለም፣ በሃይማኖት፣ በጾታ፣ በትውልድ አገር ፣ በአካል ጉዳት፣ በዕድሜ፣ ወይም በዘረግንድ መረጃ ላይ መሠረት አለማድረጉን ማረጋገጥ።

▪ የሥራ መመሪያዎች እና ተግባራት ከሥራ ጋር የተያያዙ መሆናቸውን እና የተወሰኑ ሰዎችን በዘር፣ በቆዳ ቀለም፣ በሃይማኖት፣ በጾታ፣ በትውልድ አገር፣ በካል ጉዳንት፣ ወይም በዕድሜ ምክንያት ያለአግባቢ እንዳያገላቸው ማረጋገጥ።

▪ ሠራተኞች ከዘራቸው፣ ከቆዳ ቀለማቸው፣ ከሃይማኖታቸው፣ ከጾታቸው፣ ከትውልድ አገራቸው፣ ከአካል ጉዳተኝነታቸው፣ ከዕድሜአቸው፣ ወይም ከዘረግንድ መረጃቸው የተነሳ ክብራቸው የማይነካ መሆኑን ማረጋገጥ።

▪ ሕግን መሠረት ባደረገ መልኩ የክፍያ ልዩነት ካላሳመኑ በስተቀስ፣ ተመሳሳይ ሥራ ለሚሠሩ  ለወንድ እና ለሴት ሠራተኞች እኩል የሆነ ክፍያ መፈጸም።

▪ መድልዎ እንደደረሰባቸው ቅሬታ ለሚያቀርቡት በፍጥነት እና ተገቢ በሆነ ሁኔታ ምላሽ መስጠት።  ክብረነክን እና መድልዎን ማስቆም፣ መፍትሔ መስጠት፣ እና መከላከል። ሠራተኞች ቅሬታ ስላቀረቡ አለመቀጣታቸውን ማረጋገጥ።

▪ ተገቢ የሆነ ለሥራ የሚመሆኑ ነገሮችን ( በሥራ ቦታ ላይ ነገሮች በተለምዶ ከሚሰሩበት ቦታ ላይ ለውጦችን ማምጣት፣ ማለትም እንደ ሠራተኛው ከሃኪሙ ጋር ያለውን ቀጠሮ  መከታተል እንዲችል ወይም ሃይማኖታዊ የበዓል ቀኖችን እንዲያከብር የቀጠሮ ለውጦችን መፍቀድ) በሕግ የሚጠየቅ ከሆነ፣ ለህክምና ወይም ለሃይማኖታዊ ምክንያቶች ለሚፈልጉ ለአመልካቾች እና ለሠራተኖች  መስጠት።

▪ የፌደራል የሠራተኞች መድልዎን የሚከላከሉ ሕጎችን የሚገልጸውን ፖስተር መለጠፍ (አንዱን በነጻ ከዚህ http://www1.eeoc.gov/employers/poster.cfm ድኅረገጽ ላይ ያውሩዱት)።

▪ በሕግ እንደተደነገገው የሠራተኛን መዝገቦች (ማለትም ማመልከቻዎችን ወይም የሠራተኛው መዛግብቶችን) በአግባብ መያዝ

በፌዴራል፣ በግዛት፣ ወይም በአከባቢው ሕጎች ተጨማሪ ኃላፊነቶች ሊኖርዎት ይችላል።

## እንዴት ሊንረዳ እንችላለን

▪ ተግባራዊ ስላደረግናቸው ሕጎች ያልዎትን **ጥያቄዎች መመለስ እንችላለን።**

▪ ክብረነክን፣ መገለልን፣ እና ሌሎች ሕጋዊ ያልሆኑ የመድልዎ ቅርጾችን እንዲከላከሉ እርስዎን ለመርዳት **ሀሳቦችን ሊንሰጥ እንችላለን።**

▪ ስለ ሥራ ቦታ መብቶች እና ኃላፊነቶች **እርስዎን እና ሠራተኞችዎን ማሰልጥን እንችላለን።**

▪ በሽምግልና **የEEOC የመድልዎ ቅጣቶችን (ቅሬታዎችን) በመፍታት ሊንረዳዎት እንችላለን።** የEEOC ሽምግልና ከክፍያ ነጻ፣ መደበኛ ያልሆነ፣  ጊዜዎትን እና ገንዘብዎትን ሊያድን የሚችል ለሙግቶች መፍትሔ ለመስጠት ሚስጥራዊነቱ የተጠበቀ ሂደት ነው።

### ይደውሉልን!

**በአገሪቱ ውስጥ ያለ የEEOC ሠራተኞች እርስዎን ለመርዳት አሉ። አይዘግዩ፤ ዛሬውኑ ይደውሉልን!**
አስፈላጊ ከሆነ፣ ከክፍያ ነጻ የሆነ የቋንቋ እርዳታ የሚሰጡ ይገኛሉ፤

▪ ***ስለ የEEOC መረጃ ወይም ስልጠና ይፈልጋሉ?***
በአካባቢዎ የሚገኝ የአነስተኛ ሥራዎ የ EEOC ላይሰን በዚህ (http://www.eeoc.gov/employers/contacts.cfm) ድኅረገጽ ላይ ያግኙ ወይም በ 1-800-669-4000 (TTY: 1-800-669-6820) ይደውሉልን።

▪ ***የግድ ስለሚንላቸው ሕጎች መረጃ ይፈልጋሉ?***
በ(202) 663-4691 ላይ ይደውሉልን ወይም።

▪ ***በሥራዎ ላይ ስለመጣው ስለ EEOC የመድልዎ ቅጣት ጥያቄዎች አልዎት?***
ለእርስዎ ክስ የተመደበውን የEEOC መርማሪ ያግኙ።

ከእርስዎ ለመስማት እንጠባበቃለን!

ለበለጠ መረጃ፣ የአከባቢዎን የአነስተኛ ሥራዎች EEOCን ሊይሰንን በ (http://www.eeoc.gov/employers/contacts.cfm) ያግኙ።